# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የባህል ፖሊሲ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

፲፱፺ ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ ገፅ


መግቢያ

ክፍል ፩፡- የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ራእይ፣ መርሖ እና ዓላማ

፩.፩ የፖሊሲው አስፈላጊነት

፩.፪ የፖሊሲው ራእይ

፩.፫ የፖሊሲው መሠረታዊ መርሆዎች

፩.፬ የፖሊሲው ዓላማ

ክፍል ፪፡- የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና ስልቶች

፪.፩ የቅርስ ሀብት ልማት

፪.፪ የባህል ኢንዱስትሪዎች ልማት

፪.፫ ባህላዊ ዕሴቶችና ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች

፪.፬ ባህላዊ ማንነትና ብዝኃነት

፪.፭ የባህል ተቋማት

፪.፮ ባህልና ትምህርት

፪.፯ ሕዝባዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት

፪.፰ የባህላዊ ቱሪዝም ልማት

፪.፱ የባህል ዲፕሎማሲ

፪.፲ ብሔራዊ የባህል መረጃ አያያዝና አሠራር ሥርዓት

፪.፲፩ የባህል ቅርሶችና የፈጠራ ውጤቶች ጥበቃ

፪.፲፪ የባህል ጥናትና ምርምር

፪.፲፫ ቋንቋ

## ክፍል ፫፡- የፖሊሲው አተገባበር

፫.፩ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሚና

፫.፪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ

፫.፫ የሃይማኖትና የእምነት ተቋማት

፫.፬ የግል ባለሀብቶች

፫.፭ ስለሰው ሀብት ልማት

፫.፮ ግንዛቤ ስለመፍጠር

፫.፯ የፋይናንስ ምንጭ

፫.፰ ክትትልና ግምገማ

፫.፱ የፖሊሲው አስፈጻሚ ተቋማት

፫.፲ የፖሊሲው ማስፈጸሚያ የሕግ ማዕቀፎች

## መግቢያ

ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ፈጣን እድገትና ለውጥ በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ የእድገት ዐውድ ውስጥም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብዝኃ-ባህላዊ ሀብቶች በሁሉም የልማት መስኮች የሚኖራቸውን ቁልፍ ሚና ለማሳደግና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችሏቸው ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለባህል ዘርፍ ልማት ከመቸውም ጊዜ የላቀ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ለምሳሌ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. የጸደቀው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፴፱ እና ፺፩ በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በቋንቋዎቻቸው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋዎቻቸውን የማሳደግና ባህሎቻቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኮቻቸውን የመንከባከብ መብት እንዳላቸው ደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቻቸው ተከበረው በማንነታቸው ኮርተው እንዲኖሩና ሊጋሩና ለተናጠል እድገታቸው መሠረት የሆኑ የጋራ የባህል እሴቶቻቸውን ማጎልበት እንዲችሉ ዋስትና ሰጥቷል፡፡ ለእነዚህ ሕገ መንግሥታዊ የፖሊሲ ዓላማዎች ተግባራዊነትም አስፈላጊ መዋቅራዊ መሠረቶች ተዘርግተው ወይም ተጠናክረው ተገንብተዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የሀገሪቱ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ታሪኮች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲያድጉና እንዲለሙ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

በ፲፱፻፺ ዓ.ም የጸደቀው የመጀመሪያው የባህል ፖሊሲ በርካታ የባህል ጉዳዮች የተካተቱበት የነበረ ቢሆንም አጠቃላይ ይዘቱ ግን የባህል ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳዎችና ተግባራትን አጉልቶ ካለማሳየቱም በላይ የሁሉም የልማት ዘርፎች ማዕከል የሆነው የባህል ሀብት ልማት ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶችንና የአሠራር ቅንጅቶችን በግልጽ አላመላከተም ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባህል በወቅቱ ከሚታዩት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ሊኖረው በሚችለው ቁርኝት ላይ ትኩረት የሰጠ አልነበረም፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ኀብረ ባህል የሰብአዊ እና ቁሳዊ ልማት መሠረት መሆኑን በጥልቀት በመገንዘብ ማንነታችንን፣ ብሔራዊ መግባባትንና አንድነታችንን በሚያጠናክር፣ የልማት ራእያችንንም በሚያሳካ መልክ መጠበቅ፣ ማበብ፣ መጎልበትና ለትውልድ መተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ዛሬ በምንገኝበት ዘመን በዓለማችን ከሚስተዋለው የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ መስፋፋት እና የሕዝብ ፍልሰት እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት በሀገሪቱ ባህል ላይ የሚፈጠረውን የዘመነ ሉላዊነት ተፅዕኖ መቋቋም ያስፈልጋል፡፡ መንግሥት ለባህል ዘርፍ ልማት የሰጠውን ትኩረት የበለጠ ማጠናከር፣ የሰላምና የልማት መሠረት የሆኑትን የመቻቻል፣ የመከባበርና የመወያየት እሴቶችን ማበልጸግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ለማሳካትም ጉልህ ልማታዊ ምላሽ መስጠት በሚያስችል ሁኔታና ሀገሪቱ የደረሰችባቸውን የልማት ትልሞች ሊያካትትና ሊያፋጥን በሚችል መልኩ ለመዳዝ የባህል ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ዩኔስኮ እ.አ.አ. በ፲፱፻፹፪ በሜክሲኮ ባደረገው ጠቅላላ ጉባዔው በሰጠው ብያኔ መሠረት ባህል ሁሉንም ምሁራዊ፤ ሥነ ምግባራዊ፤ አካላዊ፣ ስሜታዊና ሌሎች የሰው ልጆችን ምክንያታዊ ተግባራትና ባሕርያት አጠቃሎ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም የሰው ልጆች የሞራል፣ የተግባራትና ሌሎች የዕውቀት ዘውጎችን ለመማርና ገቢራዊ ለማድረግ ያላቸውን ብቃት ያካትታል፡፡ ባህል አንድ ማኅበረሰብ ከሌላው የሚለይበትን የአኗኗር ዘዴ፣ እምነት፣ ትውፊት፣ በአጠቃላይም ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶችን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ባህል በተለይም በየብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ብዝኃነት ውስጥ የሚካተቱ የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ግብረገባዊ፣ ሃይማኖታዊና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሀገረሰባዊ ታሪኮች፣ ሥነ ቃሎች፤ የቤት አሠራሮች፣ አመጋገቦች፣ ልማዶች፣ አልባሳት፣ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ሥነ ጥበባዊ ሀብቶች፣ እምነቶች እንዲሁም አዳዲስ ባህላዊና የፈጠራ ተግባራትና ውጤቶችን ያጠቃልላል፡፡

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ፤ የጥንታዊና ቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት መሆኗ ከተመሰከረላቸው ጥቂት የዓለማችን ሀገራት አንዷ ነች። ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የመጡ ባህላዊ ዕሴቶቿ የሕዝቦቿ የግልና የጋራ ማንነት መገለጫ ከመሆናቸውም በላይ ነጻነቷ ለዘመናት ጸንቶ እንዲዘልቅ ታላቅ ድርሻ አበርክተዋል። እነዚህን ሀገራዊ እሴቶች ከመንፈሳዊ ሀብትነታቸው ባሻገር ድህነትን ለማሸነፍ ለተጀመረው ትግል በቁሳዊ ሀብት ምንጭነት ያላቸውን እምቅ አቅም በመጠቀም  ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ እንዲያበረክቱ ማድረግ ይገባል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፭፣ ፴፱ እና ፺፩ ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ሕገ መንግሥታዊ እውቅና በመስጠት ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውን እና ታሪካቸውን እንዲያለሙ፣ እንዲጠብቁና በማንነታቸው እንዲኮሩ፤ እኩል የመልማት ዕድል እንዲያገኙና የዜጎች መሠረታዊ መብቶች እንዲከበሩ ደንግጓል፡፡ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብቶችና የታሪክ ቅርሶች መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ግዴታ እንደሆነና መንግሥትም ሥነ ጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ እንዳለበት በግልፅ መደንገጉ ሕገ መንግሥቱ ለሀገራችን ሕዝቦች ባህል ዘላቂና ቀጣይ እድገት የሰጠውን ልዩ ትኩረት ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም እነዚህን አበረታች ሁኔታዎች ተጠቅም የዘርፉን ዕድገት ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ይገባል፡፡

በዚህ በተሻሻለው የባህል ፖሊሲ ከላይ የተጠቀሱት ዓበይት ነጥቦች ትኩረት ተሰጥቷቸው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ቀርበዋል፡

## ክፍል ፩

## የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ራእይ፣ መርሖ፣ ዓላማ

### ፩.፩ የፖሊሲው አስፈላጊነት

፩.፩.፩ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ለኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህሎችና ቋንቋዎች እኩል ዕውቅና በመስጠት እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲከበሩ፣ እንዲስፋፉና እንዲበለጽጉ፣ ታሪኮቻቸው እንዲታወቁና

በማንነታቸው እንዲኮሩ የደነገጋቸው ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በተግባር ውስጥ መገለጽ አስፈላጊ በመሆኑ፤

፩.፩.፪ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል መሆናቸው መደንገጉን በመገንዘብና በተለይ ከባህልና ቋንቋ ጋር የሚዛመዱ ስምምነቶች በቂ ትኩረት አግኝተው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ በመረዳት፤

፩.፩.፫ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በተሰጠው ብሔራዊ ኃላፊነትና ተግባር መሠረት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ብዝኃ-ባህል፣ ቋንቋዎችና ታሪኮች እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙ፣ የሀገሪቱ ሕዝቦች አብሮ የመኖር፣ የመከባበር፣ የመቻቻል፣ የመተሳሰብ፣ የአንድነትና የሰላም የጋራ ዕሴቶቻቸውን ይበልጥ እንዲያጎለብቱ፣ ለ ዲሞክራሲያዊ ብሄራዊ መግባባት፣ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተሐድሶ የበኩላቸውን ሚናና አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ለማመቻቸት የባህል ፖሊሲ ማዕቀፍ መፍጠር ወሳኝ በመሆኑ፣

፩.፩.፬ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ብዝኃ-ባህል የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የሰብአዊ ሀብት መሠረትና ምንጭ በመሆናቸው እነዚህን ሀብቶች ወደ ኢኮኖሚ ጠቀሜታ በማሳደግ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድሎችንና ቋሚ የገቢ ምንጮችን ለመፍጠር በሚያስችል ሁኔታ የሀገር ውስጥና የውጭ መዋዕለ ንዋይ መስህቦች የሚሆኑበትን አመቺ ሁኔታ ማደራጀት በማስፈለጉ፣

፩.፩.፭ የሀገሪቱን ሕዝቦች ባህላዊ ዕውቀቶች፣ ጥበቦች፣ ልማዶች፣ የእምነት ሥርዓቶች፣ ዕሴቶችና ታሪኮች በሳይንሳዊ ዘዴ በማጥናት እንዲመዘገቡ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲለሙና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

፩.፩.፮ የሀገራችንን ሕዝቦች ባህል በመጠበቅ ለሕዝቦቿ ዘላቂ እድገት ለማዋል የሉላዊነት በጎ ተፅዕኖዎችን በአግባቡ መጠቀምና በአንፃሩም አሉታዊ ተጽዕኖዎችን መቋቋም አስፈላጊነቱን በማመን፣

፩.፩.፯ የሀገራችን ሥልጣኔ፣ ታሪክ፣ ባህልና ልዩ መገለጫ የሆኑ ትውፊቶቻችንና ቅርሶቻችን ለሰላም ግንባታና ለዘላቂ እድገታችን ከማዋላቸው በተጓዳኝ ለውጭው ዓለም ሕዝቦች በሰፊው በማስተዋወቅ የሀገራችንን መልካም ገጽታ መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የባህል ፖሊሲ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል፡፡

## ፩.፪ የፖሊሲው ራእይ

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አኩሪ ባህሎች በእኩልነትና በራስ የመተማመን ዕሴቶች ጐልብተው፣ በሥነ ጥበብና በሳይንስ በልጽገው፣ የሀገሪቱ ሰላምና ነፃነት ዋልታ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊነት መገንቢያ እና የዘላቂ ልማቷ ዓምድ የሆኑበት መካከለኛ ገቢ ያላት አገር በመፍጠር ርብርብ ውስጥ ተገቢ ሚና በመጫወት የኢትዮጵያን የሕዳሴ ጉዞ ማሳካት፡፡

## ፩.፫ የፖሊሲው መሠረታዊ መርሖዎች

### ፩.፫.፩ ብዝኃነትን መቀበልና ማክበር

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በመካከላቸው የባህል፣ የቋንቋና የእምነት ልዩነት እንዳለ ማወቅ፣ መቀበልና ማክበር፤ የመቻቻል፣ የመከባበር፣ የመወያየት እና የጋራ ዕሴቶቻችንን ተወራራሽነት በማበልጸግ በልዩነት ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ አንድነትን ማጠናከር፤

### ፩.፫.፪ ባህልን መሠረት ያደረገ ማኅበራዊ ልማትን ማረጋገጥ

የሀገራችን ሕዝቦች ባህላዊ ዕሴቶችና መገለጫዎቻቸው ተጠብቀው በእኩልነትና በነጻነት እንዲለሙ ማድረግ፣ ማኅበራዊ ትስስርን ማጠናከር፣ መጤና ልማዳዊ ጐጂ ድርጊቶችን በመቋቋምና በማስወገድ የባህል እድገትን ማፋጠንና ማጐልበት፣ የሀገሪቱ ሕዝቦች ቋንቋዎች በሁሉም ማሕበራዊ መስኮች የሚኖራቸውን የአገልግሎት ደረጃ ማሳደግ፣

### ፩.፫.፫ ባህልን መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚያዊ ልማትን ማረጋገጥ

የሀገሪቱን ዘላቂ የዕድገትና የለውጥ ሂደት ለማፋጠን ባህል የምጣኔ ሀብታዊ ልማቶች መሠረት እንዲሆን መሥራት፣ የባህል ምርቶችና አገልግሎቶች ለብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት በማዋል የሀብት ማፍሪያ ምንጭ ማድረግ፣ እንዲሁም የባህል ምርቶች፣ አገልግሎቶችና ዕሴቶች ዓለም አቀፋዊ ደረጃና ሀገራዊ መለያ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

### ፩.፫.፬ ሕዝባዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን አዳዲስ የባህል ተቋማት መገንባት፣ ያሉትንም ማጠናከርና ማስፋፋት፣ ሕዝባዊ ጠቀሜታቸውን ማጎልበት፣ እንዲሁም ባህል ነክ ሙያንና ሙያተኞችን በማበረታታትና በመደገፍ በባህል ትምህርት፣ በባህል ጥበቃ፣ ጥናት ሕዝባዊ ተሳትፎን ማረጋገጥ፣

### ፩.፫.፭ አፍሪካዊ ማንነትንና ትስስርን ማጎልበት

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤትና የአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት መሆኗን አጉልብቶ ማሳየት፣ የሕዝቦቿንና የባህሏን አፍሪካዊ ገጽታና ትስስር ማጉልበት የዲፕሎማሲ ማዕከል መሆኗን መሠረት በማድረግ የአፍሪካውያን ባህሎች መናኸሪያ የምትሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሌሎች የአፍሪካ ሕዝቦችን ባህልና የባህል ውጤቶች ማስተዋወቅና የባህል ልውውጥን ማጠናከር፤

### ፩.፫.፮ ዓለም ዓቀፍ ወዳጅነትና ትብብርን ማጎልበት

ሀገራችን የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የባህል ስምምነቶች ተግባራዊ ማድረግ፤ የሀገራችንን ፍላጎትና ጥቅም መሠረት ያደረጉ አዳዲስ የባህል ስምምነቶችን ማመንጨትና ማስፈጸም፤

## ፩.፬ የፖሊሲው ዓላማ

### አጠቃላይ ዓላማ

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህላዊ ሀብቶችንና ቅርሶችን በመጠበቅ፣ በማልማትና ለሁሉም የእድገት መስኮች ግብአት በማድረግ በሀገሪቱ ሕዝቦች መካከል አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ ለመገንባትና ለማጠናከር ባህል ቁልፍ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ፡

### የፖሊሲው ዝርዝር ዓላማዎች

፩.፬.፩ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የማንነት መገለጫዎች፣ ቋንቋዎች፣ ባህላዊ ሀብቶች ማለትም ቅርሶች፣ ስነቃሎች፣ ታሪኮች፣ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች፣ ዕሴቶች እና የመሳሰሉት እንዲጠኑና እንዲሰነዱ፣ እንዲከበሩና እንዲለሙ፣ እንዲጠበቁ፣ ለዕውቀት ስርጭት ለሰላምና ለዕድገት እንዲውሉ እንዲሁም ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ፣

፩.፬.፪ የሀገሪቱን የባህል ሀብቶች በዘመኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመደገፍ ወደ ባህላዊ የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች ማሳደግ፤

፩.፬.፫ በተለያዩ መስኮች የባህል የልማት ዘርፍ በየጊዜው የሚያሳየውን እድገት ለመገምገምና ለመለካት፣ ለመቆጣጠርና ለመምራት የሚያስችል ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው አኃዛዊ የባህል መረጃ አያያዝ ሥርዓት ለመዘርጋትና በአገልግሎት ላይ ማዋል፤

፩.፬.፬ በባህል ዘርፍ የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይልና ተቋማዊ ዐቅም መገንባት፤

፩.፬.፭ ዜጎችን በማንኛውም የባህል ወይም የፈጠራ እንቅስቃሴ እና ምርት በነጻነትና በእኩልነት ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣

፩.፬.፮ በእኩልነት እና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የባህል ትብብርና ልውውጥ መፍጠርና ማጠናከር፣

፩.፩.፯ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የባህል ሀብቶች ለሀገራችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን የበኩላቸውን ቁልፍ ሚናና ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸትና ማጠናከር፣



## ክፍል ፪

## የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮችና ስትራቴጂዎች

### ፪.፩ የቅርስ ሀብት ልማት

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች በአግባቡ ታውቀው፣ ለምተውና ተጠብቀው ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማኅበራዊና ለሰብዓዊ እድገት በዘላቂነት ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ፣ እንዲሁም በነበሩበትና በሚገኙበት ሁኔታ ተጠንተውና ተመዝግበው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚከተሉት የአፈጻጸም ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

**ስትራቴጂዎች**

፪.፩.፩ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ደረጃውን በጠበቀ ሳይንሳዊ ዘዴ በየመስኩ ተጠንተው፣ ተለይተውና ተመዝግበው እንዲጠበቁና እንክብካቤና ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፣

፪.፩.፪ የሀገሪቱ ታሪክ የሀገርን ኀልውናና አንድነት፣ የሕዝቦችን ደኅንነት፣ ሰላም፣ በመቻቻል ተከባብሮ አብሮ የመኖር፣ የመተሳሰብ፣ የጋራ ተጋድሎና ጥቅም፣ መልካም ዕሴቶችን በሚገልፅና እውነተኛ ገጽታቸውን በተጠበቀ ሁኔታ ተጠንተው ይመዘገባሉ፤ ለትውልድ ይተላለፋሉ፣

፪.፩.፫ በሀገሪቱ የሚካሄዱ ማናቸውም የመሠረተ ልማት ግንባታ መርሐ ግብሮችና ሥራዎች በተለያዩ የቅርስ ሀብቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱባቸው የሚከላከል የተቀናጀ የልማት ዕቅድ አነዳደፍና አተገባበር ስልት ይቀየሳል፣

፪.፩.፬ የቅርስ አስተዳደር ሥርዓት በማበጀት የሀገሪቱ ቅርሶች ባላቸው ባህላዊና ታሪካዊ እሴትነት እና ጠቀሜታ መሠረት ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፣

፰

፪.፩.፭ ለባህልና ለቅርስ ጥናትና ምርምር የሚጠቅሙ አጋዥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀቶችንና መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለጥበቃ ተግባርና ለባህል ሥርፀት እንዲውሉ ይደረጋል፣

፪.፩.፮ በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎችና መንገዶች ከሀገር የወጡ ቅርሶች እንዲመለሱ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ይደረጋል፣

፪.፩.፯ የሀገሪቱ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችና መካነ ቅርሶችን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አኃዛዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ የሚደራጅበት ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትና ስልት በብሔራዊ ደረጃ በመንደፍ ለልማት ዕቅድ ዝግጅትና ለምርምር አገልግሎት ተደራሽ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

፪.፩.፰ ጥንታዊ የቀሻ ሥዕሎች፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ሥዕሎች፣ የብራና ጽሑፎች፣ የቀለምና የብራና አዘገጃጀቶች፣ የመጽሐፍ አጠራረዝና የአጻጻፍ ስልቶችን በመሰነድና በማጥናት የሀገሪቱን ጥንታዊ ሥልጣኔ በሰፊው የማስተዋወቅና የማልማት ሥራ ይከናወናል፣

፪.፩.፱ የከተማ ልማትና የሥነ ሕንጻ ሥራዎች የሀገሪቱን ባህላዊ ቅርሶች ትእምርታዊ ጭብጦች በዘመናዊው ግንባታ ውስጥ እንዲንፀባረቁ በማድረግ የአዲሲቱን ኢትዮጵያ ልዩ ገጽታ ገላጭ እንዲሆኑ ጥረቶች ይደረጋሉ፣

፪.፩.፲ ቅርስን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከኅብረተሰቡና ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፣

## ፪.፪ የባህል ኢንዱስትሪዎች ልማት

የባህል እንዱስትሪ ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠርና ለሀገሪቱ ልማትና ተሐድሶ ተ

ጨባጭ አስተዋጽዖ የማድረግ ዕምቅ አቅም ስላለው በባህል ሙያ ዘርፎች የልማት መርሐግብር ነድፎ ይህን አቅም ማጎልበትና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማሳካትም የሚከተሉት የትኩረት ስትራቴጂዎች ተቀምጠዋል፡፡

፱

### ስትራቴጂዎች

፪.፪.፩ በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚካተቱትን ባህላዊ ሀብቶች ሥርጭት መለየት እና በዘርፉ ልማት የገበያ እና ሌሎች ችግሮችን በጥናት እንዲለዩና መፍትሔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡

፪.፪.፪ በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ግብዓት አቅራቢዎች፣ ባለሙያዎችና አምራቾች በየተሰማሩባቸው የኢንዱስትሪ መስኮች በግልና በማኅበር እንዲደራጁ፣ የተናጠልና የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ እንዲፈቱና ጥቅሞቻቸውን እንዲያስከብሩ ይበረታታሉ፤ ልዩ ልዩ ድጋፎችም ይደረግላቸዋል፣

፪.፪.፫ እንደአካባቢው ባህላዊ ክህሎት እና የአመራረት ዘይቤ መሰረት በባህል ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ማኅበራት፣ ግለሰቦችና ተቋማት ዘመናዊና የተሻሻሉ መሣሪያዎችን መጠቀም የሚያስችላቸው ሥልጠናና ብድር ይመቻቻል፣

፪.፪.፬ የባህል ኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል፣

፪.፪.፭ የባህል ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ይደረጋል፣

፪.፪.፯ የባህል ኢንዱስትሪ ምርቶችን የገበያ ተወዳዳሪነትና ጥራት ለማሳደግ እንዲቻል አበረታች የሽልማት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪.፪.፰ በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ የፈጠራ ባለቤቶች፣ ባለሙያዎች፣ የጥሬ እቃ አቅራቢዎች፣ አምራቾች፣ አከፋፋዮች እና ሌሎች የምርትና የአገልግሎት ተዋናዮች መካከል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የምርትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤

፲

፪.፪.፱ የባህል ኢንዱስትሪን ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ማጎልበት የሚያስችሉ የባህል ኢንዱስትሪ መንደሮች ይመሠረታሉ፤ በዚህ ረገድ በተለይ የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት ጥረት ይደረጋል፡፡

፪.፪.፲ በባህላዊው የፈጠራ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በስፋት የሚስተዋለውን የጥራት ችግር ለመቅረፍ የሚያስችሉ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያላቸው የጥራት ደረጃ ምደባ መሥፈርቶችና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስልቶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይሆናሉ፤

፪.፪.፲፩ የባህል ምርቶችንና አገልግሎቶችን ሀገራዊ ባለቤትነት ማስጠበቅና ማረጋገጥ የሚያስችል መለያ እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

፪.፪.፲፪ የባህላዊ ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች የፈጠራና የተዛማጅ መብቶች ማስከበሪያ የቁጥጥር፣ የክትትል ሥርዓትና የሕግ ማዕቀፍ ተጠናክሮ ተግባራዊ ይሆናል፤

፪.፪.፲፫ ከውጭ የሚገቡና በመረጃ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚሰራጩ የባህል ኢንዱስትሪ ውጤቶች የማንነት ቀውስና አሉታዊ የባህል መበረዝን እንዳይፈጥሩ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ፪.፫ ባህላዊ እሴቶችና ሀገር በቀል ዕውቀቶች

ኢትዮጵያ የብዝኃ ባህል ሀገር ስትሆን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የጋራና የተናጠል ባህላዊ ዕሴቶቻቸውንና ባህላዊ ዕውቀቶቻቸውን ለአንድ

የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ግንባታ እንዲያውሏቸው ለማድረግ የሚያስችሉ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፤

### ስትራቴጂዎች

፪.፫.፩ የሀገራችን ሕዝቦች በሚኖሩበት መልክዓ-ምድራዊ አካባቢ ተፈጥሯዊ ሀብቶች አጠቃቀም፣ ጥበቃና እንክብካቤ፣ ስለ ብዝኃ-ሕይወት፣ ስለ አዝርዕትና ምርት፣ ስለእንስሳት እርባታ፣ ስለ ጤና አጠባበቅ፣ ስለ ባህላዊ መድኃኒቶች

ቅመማና አጠቃቀም የመሣሰሉትን ሀገር በቀል ዕውቀቶች በማጥናትና በመለየት እንዲታወቁና ለዘላቂ እድገት እንዲውሉ ይደረጋል፤



፪.፫.፪ አንድ የፖለቲካና የምጣኔ ሀብታዊ ማኅበረሰብ በመፍጠር ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚናና ድርሻ ያላቸው በተለያዩ የፎክሎር ቅርፆችና ትውፊቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ የሰላም፣ የፍትኅ፣ የእውነት፣ የእኩልነት፣ የሰብአዊነት፣ የአንድነት፣ የመተሳሰብ፣ የነጻነት፣ የመቻቻል፣ አብሮ የመኖር እና የመሣሰሉትን የሀገሪቱን ባህላዊ ዕሴቶች በማጥናት ለሰላምና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ለዲሞክራሲያዊ ብሄራዊ መግባባት፣ ለልማትና ለእድገት ግብአት እንዲውሉ ይደረጋል፤

፪.፫.፫ በሀገሪቱ የሚገኙ ትእምርተ ተምሳሌቶች እንዲጠኑ፣ እንዲመዘገቡና እንዲታወቁ በማድረግ የሕዝቦች መገለጫና ገጽታ መገንቢያ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

፪.፫.፬ የማንነት መገለጫ የሆኑት ባህሎችና ብሔራዊ ክብረ በዓላት፣ ፌስቲቫሎች፣ ዓመታዊ ልዩ ቀናት፤ አልባሳት፣ መገልገያ ቁሳቁስና የምግብ ዝግጅቶች በልዩ ልዩ መንገዶች እንዲታወቁና ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲያገለግሉ ይደረጋል፤

፪.፫.፭ የጤና ጉዳትን የሚያስከትሉ፣ የሀብትና የጊዜ ብክነትን የሚያበረታቱ፣ ስንፍናንና ጥገኝነትን የሚደግፉና የዜጎችን በራስ የመተማመን ባሕርይ የሚሸረሽሩ፣ የሳይንሳዊ ዕውቀትን ሥርፀት የሚፃረሩ ባህላዊ ልማዶችንና

የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ አመለካከቶችንና አባባሎችን በሳይንሳዊ ዘዴ አጥንቶ ለማስቀረት ወይም ለመለወጥ ዘርፈ ብዙ የባህል እድገት እንቅስቃሴዎች ይካሄዳሉ፡፡

፬.፫.፮ በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህሎች የተካበቱ የግጭት አፈታት ዘዴዎችና ዕውቀቶች፣ የግልግል፣ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓቶች እንዲጠኑና ተለይተው እንዲታወቁ እና ትውፊታዊ ማኅበራዊ ፋይዳቸውን ሳይለቁ ከዘመናዊው የግጭት አፈታት ስልት ጋር ተቀናጅተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በሕዝባዊ መድረኮች፣ በመገናኛ ብዙኃንና በትምህርት ቤቶች አማካይነት አሠራሩን ለኅብረተሰቡ የማስተዋወቅ ሥራ እንዲከናወን ይደረጋል፤



፬.፫.፯ ከኅብረተሰቡ መካከል ዕውቅናና አክብሮት የተቸራቸውን የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገረሰብ መሪዎችና አዛውንቶች፣ ወጣቶችና ሴቶች መርጦ በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችና ዕውቀቶች ላይ በማሠልጠን ለማኅበረሰባቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የማዘጋጀት ሥራ ይከናወናል፤

፬.፫.፰ በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህሎች ውስጥ የሚገኙ እና ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፤ እምነቶችና አስተሳሰቦች ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ጥበቃ እንዲያገኙ ልዩ ክትትል ይደረጋል፤

3.4.5. የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተገነባ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የባህል አካል ሆኖ እንዲዘልቅ የሚያስችል ስልት ይቀየሳል፡፡

## ፭.፩ ባህላዊ ማንነትና ብዝኃነት

የአንድ ሀገር ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ብዝኃ ባህል የማንነት መገለጫዎች ለዜጎች ታላቅ ሀብትና የማኅበራዊ ስብዕና መሠረቶች

ናቸው፡፡ እነዚህን ከጥፋት በመታደግ፤ ማጎልበትና ለዘለቄታዊ ልማት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ባህል የቀድሞውን ሥልጣኔ እንደፈጠረ ሁሉ የዛሬውን የልማት ጥረትም ማገልገል ይጠበቅበታል፣ የነገውንም ትወልድ የመቅረፅ ሚና ይኖረዋል፡፡ እነዚህን ልማታዊና ማኅበራዊ ፋይዳዎች እውን ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡

## ስትራቴጂዎች

፪.፬.፩ ሰዎች በባህላዊ ማንነታቸው እንዲከበሩና እንዲኮሩ፤ በባህላዊ ማንነታቸውና መገለጫዎቻቸው ሳቢያ አድልዎና መገለል እንዳይደርስባቸው የመከላከልና የጥበቃ ሥራ ይካሄዳል፤

፪.፬.፪ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ሕገ መንግሥቱ ባጎናጸፋቸው መብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባህላዊ መገለጫዎቻቸውን ማለትም ቋንቋ፤ ሃይማኖት፤ ባህላዊ እምነትና የሕይወት ፍልስፍና፣ ወግ፣ ልማድ፤ ባህላዊ ቅርስ፤ አልባሳት፣ መገልገያ ቁሳቁሶችና የምግብ



ዝግጅት፣ ማኅበራዊ ሥነ-ምግባርና ዕሴት በነጻነት የሚከናወኑበትና የሚበለፅጉበት ሁኔታ በይበለጥ ይጐለብታል፤

፪.፬.፫ በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች መካከል መከባበር እና ልዩነቶችን በመቀበል ተግባብቶ የመኖር ዴሞክራሲያዊ ባህልን የማጠናከር ሥራ ይከናወናል፤

፪.፬.፬ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ተሰባጥረው በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ተወራራሽ የባህል ዕሴቶቻቸውን በማጎልበት በመቻቻልና በመከባበር ለሀገር ልማትና ብልጽግና በጋራ እንዲቆሙ ለማስቻል ጥረቶች ይደረጋሉ፤

፪.፬.፭ የኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት፣ ብሔራዊና አካባቢያዊ መዘከሪያ ቀናት የሚታሰቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

## ፪.፭ የባህል ተቋማት፣

የባህል ሙያ መስኮች እንዲበለጽጉና ለሙያው እንዲሁም ለሀገር እድገት የላቀ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችሉ ተቋማትንና አሠራሮችን ማደራጀት፣ የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ አቅማቸውን ማጎልበትና ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችላቸውን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አዳዲስ የባህል ተቋማትን ለማዋቀርና ነባሮቹንም ለማጠናከር የሚከተሉት የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፭.፩ የማንነት መገለጫዎችና የብዝኃነት መሠረት የሆኑት ማኅበራዊ ተቋማት ከዘመናዊው አሠራር ስልቶች ጋር ተጣጥመው አገልግሎት መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ፤ እንዲያድጉና እንዲጠናከሩ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ ይደረጋል፤



፪.፭.፪ በሥነ ምግባር የታነጸ፣ ለሀገሩ የሚቆረቆር፣ በሥራና በቁጠባ ባህል የታነጸ ትውልድ በመፍጠር ሂደት ወሳኝ ሚና የሚያበረክቱ ትውፊታዊ ተቋማት ይበረታታሉ፤ ድጋፍም ይደረግላቸዋል፤

፪.፭.፫ የሀገሪቱን የኪነጥበባት እድገት ለማፋጠን የኪነ-ጥበባት-ምክር ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፣

፪.፭.፬ የተለያዩ የሀገሪቱ ባህላዊ ሀብቶች መገለጫዎች የሚደራጁባቸውና የሚተዋወቁባቸው ለሕፃናትና ለወጣቶች አዕምሯዊ እድገት ልዩ

ትኩረት በመስጠት የባህል ውጤቶች የሚቀርቡባቸው ተቋማት እንዲደራጁና እንዲስፋፉ ይደረጋል፤

፪.፭.፭ በተለያዩ መስኮች ባህላዊ ተቋማትን የሚመሠርቱና የሚያስፋፉ የግል ባለሀብቶች፣ ማኅበራት፣ ተቋማትና የመሣሰሉት እንዲበረታቱ ይደረጋል፤

፪.፭.፮ የምሽት የመዝናኛ ቦታዎችና የባህል ተቋማት የሀገሪቱን ባህላዊ ዕሴቶችና መልካም ገጽታዎችን የጠበቁ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

፪.፭.፯ ተቋማዊ አደረጃጀቶችንና የአሠራር ስልቶችን በመዘርጋት በባህል ልማት ዘርፎች ሕዝባዊ ተሳትፎንና ተጠቃሚነትን ለማጎልበትና ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፤

፪.፭.፰ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችን ባህላዊ ስፖርቶችና ጨዋታዎች በማጥናትና ድጋፍ ሰጪ ማዕከላትን በማቋቋም የሚለሙበትና በሠፊው አገልግሎት ላይ የሚውሉበት አሠራር ይዘረጋል፤

፪.፭.፱ በተለያዩ የሀገራችን የባህል መስኮች ላይ ጥናት የሚያካሂዱ የምርምር ተቋማት እንዲቋቋሙ፣ ያሉትም እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል፤

፪.፭.፲ ነባር የባህል ትምህርት ተቋማት ተጠናክረው እንዲቀጥሉና አዳዲስ የባህል ትምህርት ተቋማት እንዲመሠረቱ እና እንዲስፋፉ ይደረጋል፤



፪.፭.፲፩ ሥነ ጥበባዊ የፈጠራ ባህል እንዲስፋፋና እንዲበለጽግ፣ ስለ ሥነ ጥበብ የሕዝብ አጠቃላይ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲዳብርና የጥበብ ውጤቶችን የማጣጣም ባህል እንዲጎለብት የሥነ ጥበባት ውጤቶች ለምሳሌ፡- የመጻሕፍት፣ የሥዕሎች፣ የፎቶግራፎችና የቅርጻ ቅርጽ ዐውደ ርዕዮች በየጊዜው በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የሚካሄዱባቸው ማዕከላት

ይደራጃሉ፤ ይህን በቋሚነትና በመደበኛ መርሐግብር መሠረት የሚያደራጁ አካላት ይቋቋማሉ፣

፪.፭.፲፪ የንባብ ባህልን ለማሳደግ የመረጃ ምንጭ የሆኑ ንባብ ቤቶች፤ አብያተ መጻሕፍት በግለሰብ፤ በማኅበረሰብ፤ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠናከሩና አዳዲስም እንዲገነቡ ይደረጋል፤

## ፪.፮ ባህልና ትምህርት

ትምህርት ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ ሰፊውን የባህል ሀብታችንን በዘላቂነት ተጠብቀው ለሕዝቡ ዘላቂ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ለማድረግ የባህልና የትምህርት ትስስር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፮.፩ የሕዝቦች ታሪክ፣ ባህልና የባህል ሙያዎች በተለያዩ ደረጃዎች በሚገኙ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ውስጥ ገብተው ትምህርትና ሥልጠና እንዲሰጥባቸው ይደረጋል፤

፪.፮.፪ የባህል ግንዛቤን ለማሳደግ የሀገሪቱን ባህሎች የሚያንጸባርቁ ቋሚ የመገናኛ ብዙኃን ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ይደረጋል፤



፪.፮.፫ በተለያየ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባህላቸውን እንዲያውቁ፤ እንዲማሩና በባህላቸው እንዲኮሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

፪.፮.፬ በአጠቃላይ ትምህርት ሕፃናትና ወጣቶች የሥነ ጥበባት ትምህርቶች የሆኑትን ሥነ ጽሑፍ፣ ሙዚቃ፣ ዜማ፣ ዳንስ፣ ድራማ፣ ሥዕልና ዕደ ጥበባት የመሳሰሉትን እንዲቀስሙ በሥርዓተ-ትምህርት እንዲታቀፉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

፪.፮.፭ በመደበኛ ትምህርት ተቋማትና መደበኛ ባልሆኑት ውስጥ ባህላዊ የሥነጥበብ ክበቦችን የማደራጀት፣ የመደገፍና በብዝኃነት ውስጥ አንድነትን መሠረት ያደረገ የሥርፀት ሥራ ይከናወናል፡፡

## ፪.፯ ሕዝባዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት

የባህል ሀብት የባለቤቱን ይሁንታ አግኝቶ ሲለማ ሰፊ ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ለዚህም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህላቸውን በማልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፯.፩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህላቸውንና የባህል መገለጫዎቻቸውን ለመለየት፣ ለማልማት፣ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና ከባህል ውጤቶቻቸው በፍትኀዊነት ለመጠቀም የሚያስችሏቸው አደረጃጀቶችን እንዲመሠርቱ ይበረታታሉ፤ ድጋፍም ይደረግላቸዋል፤

፪.፯.፪ በባህል ዘርፍ ሕዝባዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማጎልበት የሚያስችል ተቋማዊ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪.፯.፫ ልዩ ልዩ አትራፊ ያልሆኑ ባህላዊ ተቋማትን የሚያቋቁሙና የሚያስፋፉ ባለሀብቶች፣ ማኅበራት፣ ተቋማትና የመሣሰሉት ይበረታታሉ፤

፪.፯.፬ የሥነ ጥበብና የዕደ ጥበብ ውጤቶችን፣ ጥንታዊ መጻሕፍትንና መዛግብትን በግል ተነሳሽነትና ሕጋዊ መንገድን ተከትለው ለሚያሰባስቡ ወይም በአደራ

ለመንግሥት ለሚያስረክቡ፣ እንዲሁም በሌሎች የባህል ዘርፎች ጠቀሜታ ያላቸው ተግባራትን ለሚያከናውኑ ድጋፍ እና ማበረታቻ ይደረጋል፤

፪. ፲፩.፫ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ትውፊታዊ ሀብቶች በልዩ ልዩ ዘዴዎች ከጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ፣ ቀጥተኛ ባለቤት የሆነው ሕዝብ ጥቅም እንዲጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪.፲.፫ ዜጎች በተለያዩ የባህል ዘርፎች በፈቃደኝነት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱባቸው ክበባት፤ የሙያና የብዙኃን ማኅበራት እንዲያቋቁሙ ይበረታታሉ፤

## ፪.፭ የባህላዊ ቱሪዝም ልማት

በሀገራችን እስካሁን ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙት ባህላዊ፤ ታሪካዊ፣ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ቅርሶች በርካታ ባለመሆናቸው ሀገሪቱ ያላትን እምቅና ግዙፍ የባህል ሀብት ለባህላዊ ቱሪዝም አገልግሎት ለማዋል የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፭.፩ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች በጥናት በመለየትና በማደራጀት ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል፤

፪.፭.፪ የባህል ኢንዱስትሪ ውጤቶች የሆኑት የስጦታ ዕቃዎች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ ሆነው ለሀገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ እንዲቀርቡ የማማከር፣ ገበያ የማመቻቸትና የመደገፍ ሥራዎች ይከናወናሉ፤

፪.፰.፫ በቅርሶች፣ በመካነ ቅርሶች፣ በታሪካዊ ቦታዎችና በባህላዊ የእምነት ተቋማት ላይ በቅርሱ ባለቤቶችም ሆነ በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከሚደርሱ ልማዳዊ፣ ማኅበራዊ፣ አካላዊና ከባቢያዊ ጉዳቶች ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪.፰.፬ በባህላዊ ቱሪዝም ሳቢያ የሀገሪቱ ሕዝቦች ባህላዊ ማንነት እንዳይሸረሸር፤ ሰብአዊ ክብራቸውና ልማታቸው እንዲጣጣም ይደረጋል፡፡

፪.፱.፯ በሀገራችን በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎችና ከተሞች ቋሚ ኤግዚብሽኖች እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣

፪.፰.፭ የባህላዊ ቅርሶችን የቱሪስት መስህብነት በጥናት የመለየት፣ የማልማት፣ የማደራጀትና የማስተዋወቅ ሥራ ይከናወናል፤

## ፪.፱ የባህል ዲፕሎማሲ

የባህል ዲፕሎማሲ በሕዝቦች መካከል የሚፈጠር የባህል ልውውጥን፣ ትብብርን፣ ማስተዋወቅንና አጋርነትን የሚያካትት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ነው፡፡ የባህል ዲፕሎማሲ በሀገራችን ሕዝቦችና በሌሎች ሀገራት ሕዝቦች መካከል መግባባትን፣ መተማመንና መደጋገፍን በማበረታታት በሕዝቦች መካከል ወዳጅነት፣ ጠንካራ ግንኙነትና ትስስርን ለመፍጠር እንዲቻል ጥንታዊ ሥልጣኔዎችንና አኩሪ ባህላዊ ዕሴቶችን ለውጪው ዓለም በማስተዋወቅ ለሕዝቦቻችን አዎንታዊ እይታና አጋርነትን ለማጠናከር እንዲቻል የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፱.፩ የሀገሪቱን ጥቅምና ፍላጎት ያማከለ የባህል ትብብር፣ አጋርነት፣ ልውውጥና የማስተዋወቅ ስልት ተነድፎ ከጎረቤት አገሮች፣ ከአኅጉራችንና ከሌላው ዓለም ሕዝቦች ጋር ወዳጅነታችንን የሚያጎለብቱ ዓለም አቀፋዊ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች ይከናወናሉ፤

፪.፱.፪ ባህላችንን የሚያስተዋውቁ አርቲስቶችን፣ ደራሲዎችንና ሌሎች የሥነ ጥበብ ሙያተኞችን በውጪው ዓለም ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የማስተዋወቅና የማስተሳሰር ተልእኮ ያላቸው ተግባራት ይከናወናሉ፤

፪.፱.፫ የሕዝቦችን የእርስ በእርስ ግንኙነት የሚያጠናክሩ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የባህል ፌስቲቫሎች፣ የውይይትና የትውውቅ መድረኮች፣ ጉባኤዎችና በተለይ አፍሪካዊ ማንነትን የሚያስተዋውቁ ባህላዊ ምርቶችና አገልግሎቶች በመርሐግብር እንዲዘጋጁ ይደረጋል፤

፪.፱.፬ የኢትዮጵያ ወዳጆች ማኅበራትን በተለያዩ የዓለም ሀገራት በማቋቋም የባህል ዕሴቶቻችንና ሀብቶቻችን ሰፊ ትውውቅ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣

፪.፱.፭ በሀገር ውስጥ የሚዘጋጁ ፊልሞች እና ሌሎች የፈጠራ ስራ ውጤቶች የሀገሪቱን ገጽታ የሚያስተዋውቁ እንዲሆኑ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፣

፪.፱.፮ በውጭ ሀገር የሚገኙ ኤምባሲዎቻችን የባህል ጉዳይ የሚከታተሉ ሙያተኞች እንዲኖራቸው ተገቢው ጥረት ይደረጋል፣

፪.፱.፯ ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆኑ ማኅበረሰቦች በሀገራችን የባህል ዲፕሎማሲ ሥራችን ገንቢ ሚና እንዲኖራቸው አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል፣

፪.፱.፱ የኢትዮጵያን ባህል የሚያስተዋውቁ የኅትመት እና የፈጠራ ሥራዎችን በማዘጋጀት ወደ ውጭ ለሚጓዙ ኢትዮጵያዊያን ተደራሽ ይደረጋል፣

፪.፱.፲ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሀገራችን የባህል አምባሳደር ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ድጋፍና ማበረታታት ይደረጋል፣

## ፪.፲ ብሔራዊ የባህል መረጃ አያያዝና አሠራር ሥርዓት

የባህል ዘርፉ ካለው ስፋትና ባሕርይ አኳያ ባህላዊ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚደራጅበት የአሠራር ዘዴና የውጤት መለኪያ መሥፈርት የሚወጣበትና ክትትልና ድጋፍ የሚያገኝበት ሥርዓት ከመዘርጋት አስፈላጊነት አኳያ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፲.፩ ብሔራዊ የባህል መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋትና ለማቋቋም የባሕል ልማት ዘርፍ መደቦች ተጠንተውና ተለይተው በብሔራዊ ደረጃ ምደባ ይደረጋል፤

፪.፲.፪ ብሔራዊ የባህል መረጃ ሥርዓት መዘርጋትና ማቋቋም የሚያስችሉ ዘመናዊ አኃዛዊ የአሠራርና የአጠቃቀም ዘዴዎች ይጠናሉ፡፡ ሳይንሳዊ ስልቶችና አሰራሮች ተነድፈውና ተደራጅተው በተግባር እንዲውሉ ይደረጋል፤

፪.፲.፫ የጥንታዊ ባህል መረጃዎች፣ የባህል ኢንዱስትሪ የፈጠራ ውጤቶችና ባህል ላይ ያተኩሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲሰባሰቡ፣ እንዲታተሙ፤ ተደራጅተው እንዲያዙና በቀላሉ ተደራሽና ለተለያዩ የልማት ሥራዎች አገልግሎት እንዲውሉ ይደረጋል፤

## ፪.፲፩ የባህል ቅርሶችና የፈጠራ ውጤቶች ጥበቃ

የባህል ቅርሶች ተበታትነው በመገኘታቸውና የፈጠራ ኢንዱስትሪ ምርቶችም የአእምሮ ውጤት በመሆናቸው ከሌሎች ጥረቶች በተጓዳኝ የሕግ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህም ተፈጻሚነት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፲፩.፩ ምትክ የሌላቸው የሀገር ቅርሶች እንዳይሰረቁ፣ እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡና ከሀገር እንዳይወጡ፣ እንዲሁም ሕገወጥ በሆነ ማናቸውም ዘዴ ለንግድ ሥራ ማስታወቂያ አገልግሎት እንዳይውሉ የሚከለክሉ ነባር ሕጎች ተፈፃሚነታቸው እንዲጠናከርና አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ሕጎችም እንዲወጡ ይደረጋል፤

፪.፲፩.፪ በተለያዩ መንገዶችና ታሪካዊ አጋጣሚዎች ከሀገር የወጡ ቅርሶችን ለማስመለስ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪.፲፩.፫ የፈጠራ ሥራ ባለቤትነትንና ተዛማጅ መብቶችን የሚያስከብሩ የሀገሪቱ ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ፣ ከቴክኖሎጂው እድገት ጋር የሚጣጣሙ አዳዲስ ሕጎች እንዲቀረፁና የአሠራር ሥርዓቶች እንዲዘረጉ ይደረጋል፤

፪.፲፩.፬ ታሪካዊ ዋጋ ያላቸውን ሰነዶችና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በማዕከልና በክልላዊ መካነ መዛግብትና ሙዚየሞች በአደራ የሚያስቀምጡ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ድርጅቶች ያላቸውን የአደራ ሰጪነትና ለመንግሥት የማስተላለፍ መብትና ጥቅም የሚያስከብር ሕግና አሠራር ይዘጋጃል፤

## ፪.፲፪ የባህል ጥናትና ምርምር

በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ተደግፈው የሚቀርቡ ሥራዎች ለባህል ዕድገት፣ልማትና ጥበቃ፣ በእውቀት ላይ ለተመሠረተ የፖሊሲ አቅጣጫና ስኬታማ ተግባር ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው በመሆኑ ለዚህ ተፈጻሚነት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡

### ስትራቴጂዎች

፪.፲፪.፩ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የጋራና የግል ማንነት መገለጫ ባህላዊ ባሕርያት ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳዩ ደረጃቸውን የጠበቁ ሳይንሳዊ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ይከናወናሉ፤

፪.፲፪.፪ የተለያዩ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ሥነ ቃሎች፣ በቃል የሚተላለፉ ታሪኮች፣ ዕውቀቶች፣ ዕሴቶች እንዲጠኑና ለጥቅም እንዲውሉ ጥረት ይደረጋል፤

፪.፲፪.፫ የአገር ውስጥ እና ከውጭ የሚመጡ ተመራማሪዎች የሀገሪቱን የምርምር አቅም በሚያጠናክር መልክ ሥራዎቻቸውን የሚያከናውኑበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

፪.፲፪.፬ በሀገራችን ባህል ላይ የተከናወኑ የጥናትና ምርምር ውጤቶች ቅጂዎች

በሚመለከተው ሀገራዊ ተቋም እንዲቀመጥ እና አግባብ ባለው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፣

፪.፲፪.፭. በቅድመ ታሪክና በፖሊዮንቶሎጂ ጥናትና ምርምር ኢትዮጵያዊያን በስፋት እንዲሳተፉበት ለማድረግና የመስክ ተመራማሪዎችን ለማፍራት የሥልጠና ዕድሎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፣

2 21.6 በአደጋ ውስጥ ያሉ የባህል ዕሴቶች እንዳይጠፉ እና እንዲያንሰራሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ይካሄዳሉ፣ ምቹ አሰራርም ይቀየሳል፣

**፪.፲፫ ቋንቋ**

የሀገራችን ልዩ ልዩ የድምፅና የምልክት ቋንቋዎች ተጠብቀውና ለምተው የትምህርት፣ የሥራ፣ የሥነጽሑፍ፣ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ እንዲሆኑ ለማስቻል ሕገ መንግሥታዊ የቋንቋ መብቶችን ተግባራዊነት የሚያመቻች የቋንቋ ፖሊሲ ራሱን ችሎ ይቀረፃል፡፡



## ክፍል ፫

## የፖሊሲው አተገባበር

**፫.፩ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሚና**

፫.፩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የባህል ፖሊሲው ዋና አስፈፃሚ ይሆናል፡፡

፫.፪ ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማትና የመስተዳድር እርከኖች ሕገ መንግሥቱን እንዲሁም ሥልጣንና ተግባሮቻቸውን መሠረት በማድረግ ከአስፈፃሚው ሚኒስቴር መ/ቤት ጋር በመመካከርና በመቀናጀት ፖሊሲውን ያስፈፅማሉ፡፡

**፫.፪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት አስተዋፅኦ**

**የሲቪል ማህበራት**

፫.፪.፩ የሲቪል ማኅበረሰቡ በባህል ዘርፍ በንቃት እንዲሳተፍና ባህሉን እንዲንከባከብ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣

፫.፪.፪ በተለያዩ ማኅበራዊ ልማቶች ውስጥ የሚሠሩ የሙያና የልማት ማህበራት የኅብረተሰቡ ባህል በልማት ትልሞች ውስጥ ትልቅ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ በቅንጅት የሚሠሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ፫.፫ የሃይማኖትና የእምነት ተቋማት

፫.፫.፩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላትና ሥነ ሥርዓቶች ጥንታዊ ገጽታቸውና ሀገራዊ ውበታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲፈፀሙ፣ የሕዝቡ ዕሴቶችና የማንነት መገለጫነታቸው እንዲጎለብትና የሀገሪቱን መልካም ገጽታ በመገንባት ረገድ የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤



፫.፫.፪ የአብያተ ክርስቲያናትን፣ የገዳማትን፣ የመስጊዶችንና የሌሎች ቤተ እምነቶችን ዕምቅ የቅርስ ሀብቶች በመጠበቅና በመንከባከብ ለትውልድ ለማስተላለፍ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

፫.፫.፫ የሃይማኖት ተቋማት መልካም ሥነ-ምግባርን በማስተማር በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማስፈን እንዲችሉ የመከባበርና የመተሳሰብ ዕሴቶችን እንዲያጎለብቱና ተከታዮቻቸውም ለሀገሪቱ የባህል ልማት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ለሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ ይደረጋል፤

## ፫.፬ የግል ባለሀብቶች

፫.፬.፩ የግል ባለሀብቶች ቴአትር ቤቶችን፣ ሲኒማ ቤቶችን፣ የሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ማሣያ ቤቶችና ሌሎች ለባህል ልማት የሚያግዙ ተቋማትን እንዲያቋቁሙ ይበረታታሉ፤

፫.፬.፪ የግል ባለሀብቶች በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ በመሰማራት ለባህል ልማት የሚጠቅሙ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን፣ መጻሕፍትንና ሌሎች የኅትመት ውጤቶችን ከውጭ በማስመጣት፣

እንዲሁም የባህል ቅርሶችን በመንከባከብ፣ በማልማትና በማስተዳደር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

፫.፬.፫ ባህላዊ አገልግሎቶችንና አግባብነት ያላቸው ውጤቶችን ወይም ምርቶችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ፡፡

## ፫.፭ ስለሰው ሀብት ልማት

ለዚህ ፖሊሲ አፈጻጸም አስፈላጊው ሰብአዊ የአቅም ግንባታ ሥራ ይከናወናል፡፡



## ፫.6 ግንዛቤ ስለመፍጠር

ስለ ፖሊሲው ዓላማ፣ ይዘት እና አፈጻጸም በተለያየ ደረጃና ስልት ተከታታይነት ያለው የሕዝብ ግንዛቤን የማዳበር፣ የማስተዋወቅ ወይም የስርጸትና የመረጃ ስርጭት ሥራ ይከናወናል፡፡

## ፫.፯ የፋይናንስ ምንጭ

የፖሊሲው ማስፈጸሚያ የፋይናንስ ምንጭ ከሚከተሉት ገቢዎች የተውጣጣ ይሆናል፡፡

ሀ. ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፣

ለ. ከብድርና ዕርዳታ፣

ሐ. ወደፊት ከሚቋቋም የባህል ትረስት ፈንድ፣

መ. ከሕዝብና ከልዩ ልዩ ምንጮች ፡፡

## ፫.፰ ክትትልና ግምገማ

፫.፰.፩ ስለ ባህል ፖሊሲው አፈጻጸም የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፫.፰.፪ የፖሊሲ አፈጻጸም ሪፖርቶች በግልጽ ከተቀመጡ መሥፈርቶች እና ከስኬት አመላካቾች አንጻር እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

## ፫.፱ የፖሊሲው አስፈጻሚ ተቋማት አደረጃጀት

፫.፱.፩ ፖሊሲውን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማስፈጸም ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተወከሉበት የባህል መማክርት ጉባዔ ይቋቋማል፤

፫.፱.፪ በባህልና ተዛማጅ መስኮች ምርምር ላይ የሚሠማራ የባህል ተቋም ይቋቋማል፡፡

## ፫.፲ የፖሊሲው ማስፈጸሚያ የሕግ ማዕቀፎች

ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ሕጎች፣ ስልቶች፣ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችና መርሐ ግብሮች፣ እንዲሁም የአሠራር መመሪያዎች እየተዘጋጁ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡